# የ WIC QR ኮድዎን እንዴት በተፈቀደላቸው

## የገበሬዎች ገበያ እና የእርሻ መደብሮች መጠቀም እንደሚችሉ

ወርሃዊ የፍራፍሬ እና የአትክልት ጥቅማጥቅሞች እንዲሁም የ Farmers Market Nutrition Program (FMNP፣ የገበሬዎች ገበያ የአመጋገብ ፕሮግራም) ጥቅማጥቅሞች በ Special Supplemental Nutrition Program for Women, Infants and Children (WIC፣ የሴቶች፣ ጨቅላ ሕጻናት እና ሕፃናት ልዩ የተጨማሪ ምግብ ፕሮግራም) QR ኮድ መጠቀም ይቻላል። እባክዎ የ ***WIC ፍራፍሬዎች እና አትክልት*** እንዲሁም ***የ Farmers Market Nutrition Program*** ድረ ገጾችን ይጎብኙ።

**የእርስዎን የ WIC QR ኮድ ለመጠቀም የሚከተሉትን ቅደም ተከተሎች ይውሰዱ፡-**



### ቅደም ተከተል 1

**የተፈቀደላቸው የ WIC ገበሬዎች ገበያ ወይም የእርሻ መደብር ያግኙ።**

**ጠቃሚ ምክር** *የእርስዎን WICSshopper መተግበሪያ ይመልከቱ ወይም በ **FMNP ድረ ገጽ ላይ ዝርዝር ይመልከቱ**።*



### ቅደም ተከተል 2

**የ WIC QR ኮድዎን እንደያዙ እርግጠኛ ይሁኑ።**

**ጠቃሚ ምክር** *የ QR ኮድዎን በስልክዎ ያንሱ እና በገበሬዎች ገበያ ወይም በእርሻ መደብር ይጠቀሙበት።*




### ቅደም ተከተል 3

**ፍራፍሬ እና አትክትልትዎን ይምረጡ።**

**ጠቃሚ ምክር** *ይህን ምልክት የሚያሳዩ አምራቾችን ይፈልጉ!*



### ቅደም ተከተል 4

**አምራቹ የእርስዎን QR ኮድ በተንቀሳቃሽ መሣሪያው ስካን አድርጎ የግዢውን መጠን ያስገባል።**



### ቅደም ተከተል 5

**የግዢዎን መጠን ያረጋግጡ እና የ WIC ካርድዎን ባለ 4-አሃዝ ፒን ያስገቡ።**

**ጠቃሚ ምክር** *የ FMNP ጥቅማጥቅሞች ከ WIC የፍራፍሬ እና አትክልት ጥቅማጥቅሞችዎ በፊት ጥቅም ላይ ይውላሉ! **ማስታወሻ፡-** ግዢዎን ለመሸፈን በቂ ጥቅማጥቅሞች ከሌልዎት በሌላ ዘዴ መክፈል ወይም ያን ያህል ላለመግዛት መምረጥ ይችላሉ።*

**እርዳታ** የካስኬድስ ድጋፍን በ 1-800-841-1410፣ የውስጥ መስመር 3 ያግኙ፣ 2ን በመምረጥ ያግኙ

DOH 964-024 April 2023 Amharic | ይህን ሰነድ በሌላ ቅርጸት ለመጠየቅ፣ ወደ 1-800-841-1410 ይደውሉ። መስማት የተሳናቸው ወይም መስማት የሚቸገሩ ደንበኞች፣ እባክዎ በስልክ ቁጥር 711 (Washington Relay) ይደውሉ ወይም በ WIC@doh.wa.gov ኢሜይል ይላኩ።